## የእመቤታችን፡ስደት

የሰብአ፡ሰገልን፡ገፀ-በረከት፤

የእረኞቹን፡የዝማሬ፡አንደበት፤

የከብቶቹን፡ሙቀት፡መስጠት፤

የመላዕክቱን፡ምስጋና፤

የካህናተ፡ሰማይን፡ጣዕመ፡ዜማ፤

የምስራቅ፡ኮከብን፡ግርማ፤

የዓለም፡ንጉሥ፡ክርስቶስን፡መወለድ፡ሲሰማ፤

ሄሮድስ፡በምቀኝነት፡ተነስቶ፤

ልጅሽን፡ሊገድል፡ካንቺ፡ለይቶ፤

እልፍ፡አዕላፋት፡ህፃናትን፡አስፈጅቶ።

ቢያስብም፡አልቀናው፡ይህ፡እቡይ፡ንጉሥ፤

መልአኩ፡ፈጥኖ፡ዮሴፍ፡ዘንድ፡ሲደርስ።

እመብርሃን፡ከሀገሯ፡ወጥታ፤

ስትገባ፡በስደት፡ተርታ፤

ዮሴፍንና፡ሶሎሜን፡አስከትላ፤

እግሯን፡ሲወጋት፡እሾህ፡አሜኬላ፤

አቤት!ድንግል፡ፀንታ፡መታገሷ፤

መከራውን፡ሁሉ፡ችላ፡ማለፏ።

ውኃ፡ቢጠማት፡አፏ፡ድርቆ፤
ረሀብ፡ፀንቶባት፡ሰውነቷ፡ደቆ፤
ጎራ፡ብትል፡ከመንደሩ፤
ለመላቀቅ፡ከችግሩ፤
ማን፡ሰምቷት፤
ማንስ፡አዝኖላት፤
እህል ውኃ፡የሚሰጣት፤
ከድካሟ፡የሚያሳርፋት፤
ትዕማንንና፡ኮቲባን፡ስታያቸው፤
ደጃቸው፡ቆማ፡ብትለምናቸው፤
ተዘከሩኝ፡ብትላቸው፤
ጥፊና፡ስድብ፡ሆነ፡መልሳቸው።
የፀሀይ፡ሀሩርን፡ችላ፤
ድምፀ-አራዊትን፡ታግሳ፤
ዝናብና፡ዶፍ፡ሲወርድባት፤
ብርድና፡ውርጭ፡ፊቷን፡ሲገርፋት፤
ስትወድቅ፡ስትነሳ፤
ግርማ፡ሌሊቱን፡አልፋ፤
እግሯ፡ሲቃጠል፡በበረሀው፡አሸዋ፤

አቤት!ድንግል፡አደራዋ፤

ያደረገችው፡ውለታዋ፤

ሂሮድስ፡እንዳይገድለው፡ጥበቃዋ፤

መድህን፡ክርስቶስን፡ለኛ፡መሸሸጓ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ

ለንደን